# ልኡካኑ የያዙትን መንገድ የሚያጸድቀው ልዑል ዓላማ አልታየኝም

ጌታቸው ኃይሌ

የቅንጅት ልኡካን በውጭ ሀገር ወደምንገኘው ኢትዮጵያውያን የመምጣታቸው ወሬ ሲሰማ ደስተኞችና ተስፈኞች ሆነን ነበር። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት ሲሉ በእስር ቤት ከማቀቁ በኋላ መፈታታቸው ብቻ ሳይሆን ልናያቸውም በመቻላችን ደስታችን ከፍ ያለ ነበር፤ የመጣነው ልናመሰግናችሁ ነው ቢሉንም፥ አመስጋኞቹ እኛ ነን፤ ተመስጋኝ እነሱ ናቸው፤ የመጡት እንድናመሰግናቸው፥ እንድናደንቃቸው፥ እንድናጨበጭብላቸው ነው። ቅንጅት በግንቦት ምርጫ የነሣው ድል በትግሬ ወያኔዎች የተደቆሰውን ሕዝብና እኛን ስደተኞቹን በነፃነት ጮራ አስተሳስሮን ነበር። የቅንጅት ልኡካን የመምጣታቸው ወሬ ሲሰማ አግኝተናቸው "እስቲ ንገሩን! እንዴት ነበር? እያልን የሚነግሩንን ለመስማት ጓጉተን ነበር።

ተስፋችን ደግሞ ፓርቲው ከሀገር ይውጣ የሚሉ ሰዎች በመጡብን ጊዜ እነሱንና ሐሳባቸውን በተቀበልነውና ባልተቀበልነው መካከል የተነሣውን መከፋፈል ያስቀሩልናል በሚለው ላይ ያተኮረ ነበር። አሁን በግልጽና በግላጪ እንደምናየው የክፍፍላችን ምንጩ እነሱ ዘንድ ሆኖ ተገኘ። ከአክብሮቴና ትላልቆች ከማድረጌ የተነሣ ስልክ ደውዬ ላነጋግራቸው ስላልደፈርኩ ስለነሱ የማውቀው ካነጋገሯቸው ሰዎች እየሰማሁ ነበር። የሚያደርጉትን ንግግር ስሰማና እኔም ትንሽ መስኮት አግኝቼም የሚሉትን ከአንዳንዶቹ በቀጥታ ስሰማ፥ አንዱ ሌላውን የሚንቅና የሚያደንቅ፥ የኛው ብጤ ሆነው አገኘኋቸው። መስኮቷን ፈልጌ ያገኘኋት አቅሜን የማያውቁ ሰዎች "እንዴት ዝም ትላለህ?" ብለው ስላደፋፈሩኝ ነበር።

"ደፍሬ ብደውል ምን ልበላቸው?"

"የእነሱ አለመስማማት በቅንጅት ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ንገራቸዋ!"

አለመስማማታቸው በታሰሩለትና ሞትም ቢመጣ ሊሞቱ በተዘጋጁለት ድርጅት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ምን እንደሆነ ጠፍቷቸው እኔ ልንገራቸው? ለእኔ አንዳች ዕውቀትና እንዳላቸው አንዳች ምልክት ሳላይ ብቅ ብቅ ብል "ቀድሞ አንተ ማነህ?" ቢሉኝስ! አንድ ሰው ባለጉዳዩ "ተሰሚ ነህ" ይለዋል እንጂ ራሱ ተሰሚ ነኝ ወይም ሌሎች ተሰሚ ነህ ቢሉት ለአገልግሎት አይበጅም። በዚያ ላይ "ገንዘብ መሰረቁ ሳይረጋገጥ አራምባና ቆቦ ሆናችሁ እየተቀባበላችሁ የተከበረ ሰው ስም አታጥፉ" በማለቴ ቀና አስተሳሰብ እንደሌለኝ ሳልገምት እንዳልቀረሁ ዐውቃለሁ። እንዳየሁት ችግራቸውን የሚያውቁቱ እነሱ ናቸው፤ ራሳቸው በድርጅቱ ሥርዓት ተነጋግረው በአስቸኳይ መፍታት አለባቸው፤ ካልፈቱት፤ በእልህ ከቀጠሉበት የሚሆነውን ያውቃሉ።

በዚህ ሰሞን የሚወራው ወሬ "በማህላቸው አለመግባባት የተፈጠረው ከሥልጣን ሽኩቻ የተነሣ ነው" ስለሚለው ትንተና ነው፤ ትንተናው ማብራሪያ የጐደለው ነው። ሽኩቻው የታየው ለቅንጅት ፓርቲ ሊቀ መንበር/ፕሬዚዴንት ሲመረጥለት ከሆነ የሚጠበቅ ነገር ነው። ያ ሽኩቻ ሳይሆን ጤናማ ዴሞክራሲያዊ ውድድር ነው። ሽኩቻ አለ ከተባለ ከምርጫው በኋላ ውድድሩ ወደ ሽኩቻ ተለውጧል ማለት ነው። የሆነውና በመሆን ላይ ያለው በእርግጥ ይህ ከሆነ፥ "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" ብጤ ተሸናፊው ያመጣው ብጥበጣ እንጂ የሥልጣን ሽኩቻ አይባልም።

ሥልጣኑ የሚፈለገው ምን ክብር ለማትረፍ ነው? እንደምገምተው የቅንጅት መሪ ከመባል አያልፍም። ልኡካኑ ይዘውት የሚሄዱትን መንገድ ሳየው ደግሞ ያውም ቢሆን የሚያደርሰው ከጭቃ ሹምነት ነው። ምክንያቱም መጀመሪያ ተሰብስበው ችግራቸውን በመፍታት ፈንታ ቅንጅትን የማያዛልቅ ጉዟቸውን ቀጥለዋል። በደረሱበት ቦታ ሁሉ ሰዎች ስለተቀበሏቸውም ሳይታለሉ አልቀሩም፤ ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል እንዲሉ በፕሬዚዴንታቸው መሪነት በአንድነት ቢጎበኙን ስፍር ቍጥር የሌለው ሕዝብ እንደሚቀበላቸው ስላልገመቱ በሄዱበት የሚቀበላቸው ሕዝብ

ብዙ መስሏቸዋል፡፡ ሕዝቡ ለፕሬዚዴንታቸው ያለው አድናቂ የቱን ያህል እንደሆነ በምን ይገምቱት? እንደሰማሁት የሚቀበላቸው ሕዝብም ቢሆን አብዛኛው በዘዴና በአደገኛ ተንኮል የተሰበሰበ እንጂ ሁሉም ቋሚ የቅንጅት ደጋፊ እንዳይደለ የተነገራቸው አይመስለኝም፤ ከብዙዎቹ ተንኮሎች አንዱ ፕሬዚዴንቱ ያልመጡት ስለታመሙ ነው ወይም ተጠርተዋል የሚል ነው፡፡ ከዚህ የባሰ ተንኮልም አለ--የወያኔ የጎሳና የጎጥ ፖለቲካ እንዳለበት የተነገረኝን ወደማመን እንዳዘነብል ያደረገኝን ልናገር፤

የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ *የአማራው ሕዝብ ከየት ወደየት* የሚባለው መጽሐፍ እጄ እንደገባ ተችቼው ነበር፤ አቶ አንዳርጋቸው በአሁኑ የዲያስጶራ ጭቅጭቅ የሚጫወተውን ዋና ሚና ምክንያት በማድረግ የሰውየውን የተሳሳተ አስተሳሰብ (አሁን ቢጸጸትም) ለማሳየት ሒሴ አንዳንድ ድረ-ገጾች ላይ እንዳዲስ ወጥቶ ነበር፡፡ ያንን ሒስ ከአነበቡ ሰዎች አንዱ (ሰብለወንጌል ኢዮሴዴቅ) ከዚህ በታች ያለውን መልክት ከብዙ ቦታ ሲበትን ለእኔም ላከልኝ፤

> **From:** Seblewongel Iyosedeq [mailto: seblewongel_iyosedq@yahoo.com]
> **Sent:** Friday, August 10, 2007 4:00 PM
> **To:** UEDFHIBRET@yahoo.com; eprp_webmaster@gmail.com; ajc@anuakjustice.org; tessema_bitew@hcm.honda.com; tsegaye@hbaparking.com; yittazel@uic.edu; eeala@yahoo.com; admin@dekialula.com; editor@ethiomedia.com; media.emf@gmail.com; eliaskifle@gmail.com; editor@addisvoice.com; KINIJITINFO@KINIJIT.org; kinijitna@kinijitna.org; comments@kinijitdc.org; euafkinijit@googlemail.com; kinijitsouthafrica@gmail.com; info@kinijit.ca
> **Subject:** Dr. Getachew Haile's Call for More Divide and Rule
>
> This e-mail has been sent to 2,000 Ethiopians and Friends of Ethiopia so far:
>
> Dr. Getachew Haile's rhetoric of hate for Gojjam may endanger the very existence of CUD. Most importantly, he is implanting a poisonous tree which would help Woyanne's regime to rule for ever and ever. This man was calling names... Tigreans as non-Ethiopians (this was Paul Henz used his statement in US Senate hearing), was exchanging hate letters with a monk from Gondar, and now he is on Gojjam. Please Read between the lines of this article.
> http://www.kinijit.com/static/Book%20Review.pdf
>
> For this man, democracy is all about Shewa's Kingdom. For him, Ethiopia is synonym with Orthodox Christian Shewan Amhara. He does not undestnad or not willing to accept elementary concept of democracy. Isn't the term democracy indicates a form of government where all the state's decisions are exercised directly or indirectly by a majority of its citizenry [Shewans and all other Ethiopians] through a fair elective process? However, for him it is Shewa or nothing…what a shame!
>
> **This e-mail has been sent to:**
>
> - **Ethiopian People Revolutionary Party (EPRP)**
> - **United Ethiopian Democractic Forces**

- **Anuak Justice Council, PO Box 1597, Spokane, WA 99210 USA**
- **Gojjam Development & Association in Canada**
- **The Gondar Development and Cooperation Organization - North America**
- **GOLMA**
- **Ghion Association**
- **Ethiomedia**
- **Ethiopian Review**
- **Deki-Alual**
- **EMF**
- **Kinijit- all groups**
- **Addis Voice**

አቶ ሰብለወንጌል ኢዮሴዴቅ የሚለኝ ባጭሩ በዚህ ሒስ "ጎጃምን ይጠላል፤ ለእሱ ዴሞክራሲ ማለት የሸዋን መንግሥት ነው" ነው:: በሒሱ ውስጥ ጎጃምን ያጥላላሁበትና የሸዋን መንግሥት ያገነንኩበት ቃል የቱ እንደሆነ ለመፈለግ ሒሱን ደጋግሜ አነበብኩት፤ ምንም ነገር አላገኘሁበትም:: ለራሴ ፈራጅ እንዳልሆን በማለት እውነቱን ሊነግሩኝ የማይፈሩኝን ወዳጆቼንና ሌሎችንም አስተያየታቸውን የማከብር ሰዎች ፈልጌ በሒሱ ውስጥ ሊያስወቅሰኝ የሚችለውን ቃል እንዲፈልጉልኝ ጠየቅኋቸው:: ምንም የሚያስወቅስ ነገር እንዳላገኙበት የማውቀውን አረጋገጡልኝ:: ይኸንን ጽሑፍ ከምታነቡት ውስጥም ሒሴን ያነበባችሁ ትኖራላችሁ:: የናንተም ፍርድ የተለየ እንደማይሆን እገምታለሁ:: ወሬኞቹና ስም አጥፊዎቹ ድረ-ገጾች ሳይቀሩ ሳያወጡለት መቅረታቸው የአቶ ሰብለወንጌል ተንኮል ለእነሱ እንኳን ዝቅተኛ ነገር እንደሆነባቸው ያስረዳል::

ሰብለወንጌል የጻፈውን እያነበብኩ ሳሰላስል ጽሑፉ አንድ ነገር አስታወሰኝ፤ አንደኛ፥ የትግሬ ወያኔዎች የጎሳ ፖለቲካቸውን አፍና ብዕር አውጥቼ ስለተቃወምኳቸው ትግሬ የሚጠላ አንኮበሬ የሚል ስም አውጥተውልኝ ስለነበረ፥ ስለ ኢትዮጵያ የምጽፈውን ብዙ ትግሬዎች እንዲጠሉት ማድረጋቸውን፤ ሁለተኛ፥ በአሜሪካ ተፈጠረ የተባለውን ሲኖዶስ በመቃወሜ፥ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ አይገፉ በማለቴ፥ ለቀድሞው ፓትርያርክ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ታዛዥ የቤተ ክርስቲያን ልጅ ለመሆን በመጣሬ፥ ከጎንደር አካባቢ የተሰደዱ ጳጳሳትና ካህናት ዘረኛ የሚል ስም አውጥተውልኝ ስለነበረ ስለ ቤተ ክርስቲያኔ የምጽፈውን ብዙ የጎንደር ልጆች እንዲጠሉት መጣራቸውን:: አሁን ደግሞ የቅንጅት ፓርቲ ከኢትዮጵያ አይወጣም ከሚሉ ጋር ወግኜ ስለምጽፍ ሰብለወንጌል "አደረገ" የተባልኩትን በማስረጃነት እየዘረዘረ፥ "ጎጃምን ይጠላል" ብሎ ስሜን በመበከል ጎጃሜዎች የምጽፈውን እንዳይቀበሉ ለማድረግ ሞከረ::

ሰብለወንጌል ብቸኛ ፋኖ ቢሆንና የምጽፈውን ጎጃሜዎች እንዳይቀበሉ በማድረግ ቢወሰን ጉዳቱ በዚያው ልክ ውሱን ይሆን ነበር:: እየሆነ ያለው ግን ይኸ አይደለም፤ ሰውየው ከኋላው ሌሎችሰዎች አሉት፤ እነማናቸው? የፖለቲካቸው አዝማሚያውስ ምንድን ነው? የተፈለገው ነገር መመለስ

ከሚያዳግትበት ድረስ ርቆ ይሄዳል፤ አለመግባባት የተፈጠረው በሸዌዮችና በጎጃሜዎች መካከል የሆነ ነው የሚል ርኩስ ዓላማ ይታይበታል። የወያኔዎችን የጎሳ ፖለቲካ በመቃወም ፈንታ የሚጠቀሙበት ጉዶች የቅንጅት ደጋፊዎች ሆነው ብቅ ሳይሉ አልቀሩም። ይኸ ደግሞ የኢትዮጵያን አንድነት ለጊዜያዊ የውስጥ ጭቅጭቅ ድል መንሻ የሚያደርግ ብሔራዊ ኀላፊነት የጐደላቸው ሰዎች የሚያካሂዱት ርካሽ ፖለቲካ ነው።

ይኸንን ርካሽ ፖለቲካ ማን ያምናል? እነ ሰብለወንጌል የሚሉትን ማን ያምናል የሚል ካለ፥ አማኒ ሞልቷል። ትግሬዎችን እንደምጠላ የሚያስረዳ ነገር ማንም አላሳየኝም፤ ግን ትግሬ ይጠላል ስባል የአማኒ ችግር አልነበረም። አቡነ ይስሐቅም አቡነ ቴዎፍሎስም ሸዋ አልነበሩም፤ እነሱን በመደገፌ ዘረኛ ስባል የአማኒ ችግር አልነበረም። ክብርት ወይዘሮ ብርቱካን ሚኒያፖሊስ ላይ ባደረገችው ንግግር በቅንጅት ድረ-ገጽ ላይ ያልወጣ ነገር ወጣ ስትል ያጨበጨበላት መች ቸገራት? ያጨበጨበው ሁሉ ወጣ ያለችውን አሳየን ቢሉት ለማሳየት አይችልም። እሷ ተነግራ ተናገረች፤ አጨብጫቢዎቹ እሷን ሰምተው አጨበጨቡ። የጀሌ ሂደት እንዲህ ከሆነ ጎጃሜዎችን ይጠላል ስባል አማኝ ለምን ይጠፉል?

"ጎጃሞች ይኸንን ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ለመቀበል ምን ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል?" እያልኩ ሳጠያይቅ፥ "የዚያኛው ጎራ መሪ የጎጃም ልጅ ነው፤ የወንዙን ልጆች ማሰባሰብ ጀምሯል የሚል ጭቅጭቅ በዋሽንግተን ዲሲ ሰፍኗል" የሚል ዜና ደረሰኝ። አጋጣሚ ነው? ምኞቴ ሰብለወንጌል አጭበርባሪ ወያኔ ነው የሚለኝ ሰው ማግኘት ነበር፤ አላገኘሁም።

ልኡካኑ ያለውን ጭቅጭቅ ሲሆን ለመፍታት መሞከራቸውን አለዚያም መራቃቸውን ትተው፥ "ያንኛውን ጎራ ያዘጋጁት እነሱ ናቸው" እስኪባሉ ድረስ እዚያኛው ጎራ ሰተት ብለው ገቡ። "አብራችሁ ካልመጣችሁ አንቀበላችሁም" ወደሚባሉት አካባቢ ዓይናቸውን ጨፍነው ልባቸውን ደፍነው በእልህ ከሄዱ፥ እርምጃቸው በሀገር ጎጂ መሣሪያ ጊዜያዊ ድል ለማግኘት ነው። እውነት እንደሚባለው ልኡካኑን ከሚቀበሏቸው ውስጥ እስከዛሬ በቅንጅት ድጋፍ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ ያልነበራቸው የሰብለወንጌል ጎጃሜዎችና ጉራጌዎች ካሉባቸው የልኡካኑ ደስታ እውጪ ሀገር ተወልዶ የውጪውን ሀገር ሲለቅቁ የሚከዳቸው ነው። በሚሄዱበት ከተማ ሁሉ የሚቀበላቸው ሕዝብ መልክአ ኢትዮጵያነት ቢኖረውም ባይኖረውም ግድ የሌላቸው ከሆኑ ደስታቸው እንዴት አብሯቸው ኢትዮጵያ ይገባል?

"አብራችሁ ካልሆናችሁ አትምጡብን" የሚለው ሕዝብ እኮ ቅንጅት እንዲጠናከር የሚጥር ገለልተኛ የቅንጅት ደጋፊ እንጂ ወገንተኛው አይደለም። ለብቻችሁ አትምጡ ያለው የሲያትሉ የድጋፍ ኮሚቴማ ሊያስታርቅ ብዙ እንደጣረ ልኡካኑ ያውቃሉ። የቅንጅት ተጠሪዎች ነን የሚሉ ልኡካን እንዴት የቅንጅትን ደጋፊ ይገፋሉ? ልኡካኑ ደጋፊዎቻቸውን "ካልተስማማችሁ አንመጣላችሁም" በማለት ፈንታ "ካልተስማማችሁ አንቀበላችሁም" ሲባሉ ምን ይሰማቸዋል ስንል የአንዱ ወገን ደጋፊዎች በመሆኑ ቀጠሉበት። የተከበሩ የሕዝብ ተጠሪዎች ስለ ሆኑ የሚከበሩበት ልዩ አበል ሲገባቸው፥ ለግላቸው (አንዳንዱም በዘመድ ቀስቃሽ) የተሰበሰበ ገንዘብ ዳረጎተኞች ሆኑ።

የሚጓዙበትን መንገድ የሚያጸድቅ ልዩል ዓላማ እንዳላቸው አይታየኝም፤ የሚታየኝ ሀገራቸው ሲገቡ የመንደር ጪቃ ሹም የሚያደርግ ትሑት ዓላማ ነው።